# የእናት ሆድ ዥንጉርጉር

ካንድ ማህፀን ወጥተው
ለሰሚው ግራ ነው
የናት ሆድ ዥንጉርጉር
አንደኛው አሳማ ሌላው
የሰው ፍጡር።
አንዱ እሚለፋላት በድህነት ታንቆ
ሌላው እሚበላት ደልቶት ተንደላቅቆ
አንዱ እሚሞትላት ህይዎቱን ሰውቶ
ሌላው የሚገድላት በጦርነት ወግቶ
አንዱ እሚዋጋላት ለሉዐላዊነቷ
ሌላው የሚወጋት ደመኛ ጠላቷ
የታሪክ ጠባሳ አሉታው ተፅዕኖ
ተውፊትነቱ ውርስና ቅርስ ሆኖ
የሞተላት ቀርቶ ገዳይዋ እየበላ
ነቅዛ ተኖራለች ራሷን በድላ።

ሚያዚያ 2008

abraham beyenne